# ትምህርት 25

1. ያዕቆብን ከክፉ ሁሉ ጠብቆ ከካራን ወደ ከነዓን ምድር ያመጣው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

2. ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ የበለጠ የሚወደው ልጅ ስሙ ማን ነበር?

ሀ- ዮሴፍ።

3. ያዕቆብ ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ስለወደደው ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ ምን አሰቡ?

ሀ- በቅናት ተነሱበት ጠሉትም።

4. እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያሳየው የመጀመሪያ ሕልም ምን ነበር?

ሀ- የወንድሞቹ ነዶዎች ለዮሴፍ ነዶ ሲሰግዱ።

5. እግዚአብሔር ለዮሴፍ ያሳየው ሁለተኛ ሕልም ምን ነበር?

ሀ- ፀሐይ ጨረቃና አሥራ አንዱ ክዋክብት ለዮሴፍ ሲሰግዱ ተመለከተ።

6. የሁለቱም ሕልሞች ትርጉም ምን ነበር?

ሀ- አንድ ቀን እግዚአብሔር ዮሴፍን አለቃ እንደሚያደርገውና የዮሴፍ ቤተሰብ በሙሉ ለእርሱ እንደሚሰግዱለት።

7. የዮሴፍን የወደፊት ሁኔታ የሚያውቀውና ሊሆን ያለውን በሕልም ያሳየው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

8. ዮሴፍ በእረኝነት ስፍራ ሊጐበኛቸው በመጣበት ወቅት የዮሴፍ ወንድሞች ምን አደረጉ?

ሀ- መጀመሪያ ልብሱን ገፍፈው በደረቅ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት።

ለ- ከዚያም ዮሴፍን እንደ ባርያ ለባሪያ ነጋዴዎች ሸጡት።

9. የባሪያ ነጋዴዎቹ ዮሴፍን ወዴት ወሰዱት?

ሀ- ወደ ግብፅ።

10. የባሪያ ነጋዴዎቹ ዮሴፍን የሸጡት ለማን ነበር?

ሀ- ለጲጥፋራ።

11. ዮሴፍ የጲጥፋራ ባሪያ በነበረበት ጊዜ ምን ደረሰበት?

ሀ- የጲጥፋራ ሚስት በዮሴፍ ላይ ስለ ዋሸች ጲጥፋራ ዮሴፍን እስር ቤት አስገባው።

- እግዚአብሔር ዮሴፍን ረስቶት ነበር?

- አልረሳውም። እግዚአብሔር ማንንም አይረሳም።

- ዮሴፍ በግብፅ አገር በእስር ቤት ነበር።

- የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን በመባል ይታወቃል።

- አንድ ቀን ለፈርዖን እግዚአብሔር ሕልምን አሳየው።

ዘፍጥረት 41፥1-4

1- ድፍን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ፣ ፈርዖን ሕልም አለመ በሕልሙም፣ በአባይ ወንዝ ዳር ቆሞ ነበር።

2- እነሆም መልካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር ይበሉ ጀመር።

3- ቀጥሎም፣ መልካቸው የከፋ አጥንታቸው የወጣ፣ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው አስቀድመው ከወጡት ላሞች አጠገብ ቆሙ።

4- እነዚህ መልካቸው የከፋና አጥንታቸው የወጣ ላሞች፣ እነዚያን ያማሩና የወፈሩ ላሞች ሲውጡዋቸው አየ፤ ከዚያም ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ።

- ለፈርዖን ሕልም ያሳየው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ለፈርዖን ያሳየው የመጀመሪያው ሕልም ምን ነበር?

- ሰባት ከሲታ ላሞች ሰባት ወፋፍራም ላሞችን ሲውጡአቸው ተመለከተ።

- በዚያ ሌሊት እግዚአብሔር ለፈርዖን ሁለተኛ ሕልም አሳየው።

ዘፍጥረት 41፡5-8

5- ፈርዖንም እንደገና እንቅልፍ ወስዶት ሳለ ሕልም አየ በሕልሙም በአንድ የእህል አገዳ ላይ፣ ፍሬያቸው የተንዠረገገና ያማረ ሰባት የእሸት ዛላዎች ሲወጡ አየ።

6- ከዚያም የቀጨጨና በምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁ ሰባት የእሸት ዛላዎች ወጡ?

7- የቀጨጬት የእሸት ዛላዎች፣ ፍሬያቸው የተንዠረገገውን ሰባቱን ያማሩ ዛላዎች ዋጡአቸው። በዚህ ጊዜ ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ፤ ነገሩ ሕልም ነበር።

8- በነጋታውም፣ ፈርዖን መንፈሱ ታወከበት፤ ስለዚህ በግብፅ አገር ያሉትን አስማተኞችና ጥበበኞች በሙሉ አስጠርቶ ሕልሞቹን ነገራቸው፤ ይሁን እንጂ ሕልሞቹን ሊተረጉምለት የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም።

- እግዚአብሔር ለፈርዖን ያሳየው ሁለተኛው ሕልም ምን ነበር?

- ሰባት ቀጫጭን የእሸት ዛላዎች ሰባት ያማሩ የእሸት ዛላዎችን ሲውጡዋቸው ተመለከተ።

- ፈርዖን የግብፅ ንጉሥ ነበር ነገር ግን ፈርዖን በእግዚአብሐር አያምንም ነበር።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ ለፀሐይ ለጨረቃና ለከዋክብት ይሰግዱ ነበር።

- ፈርዖንና የግብፅ ሕዝብ ለጓጉንቸሮች ለእንስሳትና በአገራቸው ለሚፈስ ወንዝ ይሰግዱ ነበር።

- ፈርዖን በእግዚአብሔር የማያምን ሰው ቢሆንም እንኳን እግዚአብሔር የእርሱን ፈቃድ እንዲያደርግ ፈርዖንን መምራት ችሏልን?

- አዎን።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑ ሰዎች ፈቃዱን እንዲያደርጉ መምራት ይችላል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ስለሆነ እርሱ የፈለገውን እንዲያደርጉ ለሰዎች መጠቆም ይችላል።

- እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ እርሱ ከሰዎች ጋር የሚሠራው ነገር ሁሉ ፍጹም ነው።

- ሁሉም የግብፅ ጠቢባን የፈርዖንን ሕልም ፍቺ አላወቁም።

- ነገር ግን ዮሴፍ የሚባል ሰው ሕልሙን መፍታት እንደሚችል አንድ ሰው ለፈርዖን ነገረው።

- ስለዚህ ፈርዖን ዮሴፍን ከእስር ቤት እንዲመጣ መልእክት ላከለት።

ዘፍጥረት 41፡14-16

14- ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትእዛዝ ሰጠ፤ ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት መጡ፤ ጠጉሩንም ከተላጨና ልብሱን ከለወጠ በኋላ ፈርዖን ፊት ቀረበ።

15- ፈርዖንም ዮሴፍን፣ «ሕልም አይቼ ነበር፤ ሕልሜን ሊተረጉምልኝ የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም። አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመተርጐም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ» አለው።

16- ዮሴፍም ፈርዖንን፣ «እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለፈርዖን የሚሻውን ትርጉም ይሰጠዋል» አለው።

- ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም የመተርጐም ችሎታ እንሌለው ያውቃል።

- ነገር ግን ዮሴፍ እግዚአብሔር የፈርዖንን ሕልም መፍታት እንደሚችል ያውቃል።

- ዮሴፍ በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔር የፈርዖንን ሕልም ፍች ለዮሴፍ ገለጠለት።

ዘፍጥረት 41፡25-32

25- ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው፤ «ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ናቸው። እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ለፈርዖን ገልጦለታል።

26- ሰባቱ የሚያማምሩ ላሞች፣ ሰባት ዓመታት ናቸው። ሰባቱም የሚያማምሩ የእሸት ዛላዎች ሰባት ዓመታት ናቸው። ሕልሙም አንድና ተመሳሳይ ነው።

27- ከእነርሱም በኋላ አጥንታቸው የወጣ አስከፊ መልክ ያላቸው ሰባት ላሞች፣ ሰባት ዓመታት ናቸው፤ እንደዚሁም ፍሬ አልባ የሆኑትና በምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁት ሰባት የእሸት ዛላዎች ሰባት የራብ ዓመታት ናቸው።

28- «አስቀድሜ ለፈርዖን እንደ ተናገርኩት፣ እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገውን ነገር ለፈርዖን ገልጦለታል።

29- በመላው የግብፅ ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆንባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ።

30- ከዚህ በኋላ ግን በተከታታይ ሰባት የራብ ዓመታት ይሆናሉ። የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለሚጐዳት፣ በግብፅ የነበረው ያለፈው የጥጋብ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታወስም።

31- ከጥጋቡ ዓመታት በኋላ የሚመጣው የራብ ዘመን እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ፣ ቀደም ሲል የነበረው የጥጋብ ዘመን ፈጽሞ ይረሳል።

32- ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ መታየቱ፣ ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቆረጠ ስለሆነ ነው፤ ይህንንም እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ይፈጽመዋል»

- የፈርዖንን የሕልም ፍቺ ለዮሴፍ የሰጠው ማን ነበር?

- እግዚአብሔር።

- ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ፍች ምንድን ነበር?

- ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት በቀጣዮቹ ሰባት የድርቅ ዓመታት እንደሚዋጡ ተመለከተ።

- በሰባቱ የመልካም ሰብል ዓመታትና በሰባቱ ቀጣይ የድርቅ ዓመታት ምን ማድረግ እንዳለበት ዮሴፍ ለፈርዖን ሃሳብ አቀረበ።

ዘፍጥረት 41፡33-36

33- እንግዲህ ፈርዖን ብልኀና አስተዋይ ሰው ፈልጎ፣ በመላው የግብፅ ምድር ላይ አሁኑኑ ይሹም።

34- እንደዚሁም በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት፣ አንድ አምስተኛው እንዲሰበሰብ የሚያደርጉ ኃላፊዎችን ይሹም።

35- እነርሱም በሚመጡት የጥጋብ ዓመታት ከሚገኘው ምርት ሁሉ ይሰብስቡ፤ በፈርዖንም ሥልጣን ሥር ያከማቹ፤ ለምግብ እንዲሆኑም በየከተማው ይጠበቁ።

36- የሚከማቸው እህል፣ ወደፊት በግብፅ አገር ላይ ለሚመጣው የሰባት ዓመት ራብ መጠባበቂያ ይሁን፤ በዚህም ሁኔታ አገሪቱ በራብ አትጠፋም። »

- ዮሴፍ ፈርዖን በጥጋቡ ዓመታት የሚትረፈረፈውን ምርት አከማችቶ በረሃቡ ዘመን ሰዎች የሚበሉት እህል እንዲያገኙ የሚያደርግ አንድ ሰው እንዲሾም አሳሰበው።

- ፈርዖን ዮሴፍ ስላቀረበለት አሳብ ምን አሰበ?

ዘፍጥረት 41፥37-40

37- ዕቅዱንም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ መልካም ሆኖ አገኙት።

38- ፈርዖንም፣ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት እንደዚህ ያለ ሰው ማንን ልናገኝ እንችላለን?» ብሎ ጠየቃቸው።

39- ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ «እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ስለ ገለጠልህ፣ እንዳንተ ያለ አስተዋይና ብልኅ ሰው የለም።

40- አንተ በቤተ መንግሥቴ የበላይ ትሆናለህ። ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤ እኔ ከአንተ የምበልጠው በዙፋኔ ብቻ ይሆናል።»

- ፈርዖን ዮሴፍን የግብፅ ንጉሥ አደረገው።

- በግብፅ ምድር ከዮሴፍ በሥልጣን የሚበልጠው ፈርዖን ብቻ ነበር።

- ዮሴፍ በወንድሞቹ ለባርነት ቢሸጥም እንኳ እግዚአብሔር አልተወውም።

- ዮሴፍ እስር ቤት ቢጣልም እግዚአብሔር አልተወውም።

- እግዚአብሔር ዮሴፍ ትንሽ ልጅ ሳለ ያሳየውን ሕልሞች እንዴት ፈጸማቸው?

- እግዚአብሔር ዮሴፍን የመላው ግብፅ ንጉሥ አደረገው።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያቀደውን ሁሉ ይፈጽማል።

- ማንም የእግዚአብሔርን እቅድ ማስቆም አይችልም።

- ፈርዖን ዮሴፍን የግብፅ ንጉሥ ካደረገው በኋላ ዮሴፍ በጥጋቡ ዓመታት የተትረፈረፈውን ምርት በመጋዘን ማከማቸት ጀመረ።

ዘፍጥረት 41፥46-49

46- ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንን ማገልገል ሲጀምር፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር። ዮሴፍም ከፈርዖን ፊት ወጥቶ የግብፅን ምድር በሙሉ ዞረ።

47- በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ የተትረፈረፈ ሰብል ሰጠች።

48- በእነዚያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት፣ ዮሴፍ በግብፅ አገር የተገኘውን ምርት ሰብስቦ በየከተሞቹ አከማቸ፤ በእያንዳንዱ ከተማ ከየአቅራቢያው የተመረተውን እህል እንዲከማች አደረገ።

49- ዮሴፍ ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሚሆን የእህል ሰብል አከማቸ፤ ሰብሉ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ ልኩን መስፈርና መመዝገብ አልቻለም ነበር።

- በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ዮሴፍ ቁጥር ስፍር የሌለውን እህል አከማቸ።

- ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ሲያልቁ ሰባት የራብ ዓመታት ጀመሩ።

- የዮሴፍ አባትና ወንድሞች የት ነበሩ?
- በከነዓን ይኖሩ ነበር።

- በከነዓንም ድርቅ ስለ ነበር የዮሴፍ አባትና ወንድሞች ምግብ አልነበራቸውም።

- የዮሴፍ አባት ያዕቆብ እንዲህ አለ፡-

ዘፍጥረት 42፡1-5

1- ያዕቆብ በግብፅ እህል መኖሩን ሲሰማ፣ ልጆቹን እንዲህ አላቸው፣ «ለምን እርስ በርስ ትተያያላችሁ?

2- በግብፅ እህል መኖሩን ሰምቻለሁ፤ ስለዚህ ከመሞት መሰንበት ይሻላልና ወደዚያው ወርዳችሁ እህል ሸምቱልን» አላቸው።

3- ከዚያም አሥሩ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ወረዱ።

4- ነገር ግን ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን፣ ክፉ ነገር ይደርስበታል በሚል ፍርሃት ከወንድሞቹ ጋር አልላከውም።

5- ራቡ በከነዓንም በመበርታቱ፣ እህልን ለመሸመት ወደ ግብፅ ከሄዱት ሰዎች መካከል የእስራኤልም ልጆች ነበሩ።

- የዮሴፍ አባት ያዕቆብ ልጆቹ ወደ ግብፅ ሄደው እህል እንዲሸምቱ ላካቸው።

- የዮሴፍ ወንድሞች ግብፅ እንደ ደረሱ ምን ደረሰባቸው?

ዘፍጥረት 42፡6ለ-17

6- የዮሴፍ ወንድሞችም እንደ ደረሱ፣ ከፊቱ ቀርበው ወደ ምድር ለጥ ብለው እጅ ነሡት።

7- ዮሴፍም ወንድሞቹን ገና ሲያያቸው ወዲያውኑ አወቃቸው፤ ነገር ግን እንደማያውቃቸው ሆኖ፣ «ከየት የመጣችሁ ናችሁ? ብሎ በቁጣ ቃል ተናገራቸው። እነርሱም፣ እህል፣ ለመሸመት ከከነዓን ምድር የመጣን ነን» ብለው መለሱለት።

8- ዮሴፍ ወንድሞቹን ቢያውቃቸውም እንኳ፣ እነርሱ ግን አላወቁትም።

9- በዚህ ጊዜ ስለ ወንድሞቹ ያየው ሕልም ትዝ አለውና፣ «ሰላዮች ናችሁ፤ የመጣችሁት አገራችን በየትኛው በኩል

ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን ለመሰለል ነው» አላቸው።

10- እነርሱም እንዲህ አሉት፣ «ጌታችን ሆይ፤ እንዲህስ አይደለም፤ አገልጋዮችህ የመጣነው እህል ለመሸመት ነው፤

11- ሁላችንም የአንድ አባት ልጆች ነን፤ አገልጋዮችህ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደለንም።»

12- እርሱም መልሶ፣ «አይደለም፤ አገራችን በየት በኩል ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን ለመሰለል ነው» አላቸው።

13- እነርሱ ግን መልሰው፣ «እኛ አገልጋዮችህ በከነዓን አገር ከሚኖር ከአንድ ሰው የተወለድን አሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን። ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ ሲሆን፣ አንዱ ግን የለም» አሉት።

14- ዮሴፍም እንዲህ አላቸው፤ «ነገርኋችሁ እኮ፤ ሰላዮች ናችሁ።

15- ታናሽ ወንድማችሁ እዚህ እስካልመጣ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ እንደማትሉ በፈርዖን ስም እምላለሁ። ማንነታችሁ የሚረጋገጠውም በዚህ ነው።

16- በሉ፣ ከእናንተ አንዱን ላኩና ወንድማችሁን ይዞ ይመለስ፤ የቀራችሁት ግን የተናገራችሁት ቃል እስኪረጋገጥ ድረስ፣ እስር ቤት ትቆያላችሁ። እንደተናገራችሁት ካልሆነ ግን፣ በፈርዖን ስም እምላለሁ፤ ሁላችሁም ሰላዮች ናችሁ» አላቸው።

17- ሁሉንም ሦስት ቀን በእስር አቆያቸው።

- ዮሴፍ ወንድሞቹን አወቃቸው፤ ነገር ግን እነርሱ አላወቁትም።

- ዮሴፍ ወንድሞቹን የተቆጣቸውና ወደ እስር ቤት ያስገባቸው ለምን ነበር?

- ዮሴፍ ወንድሞቹ እርሱ ልጅ በነበረበት ወቅት ያደረሱበትን ነገር ንዲያስቡ ስለፈለገ ነው።

- ከሦስት ቀናት በኋላ ዮሴፍ አንዱን አስቀርቶ ሌሎቹን ወንድሞቹን በሙሉ ፈታቸው።

- ዮሴፍ ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፡-

ዘፍጥረት 42፡18-20

18- በሦስተኛውም ቀን፣ ዮሴፍ እንዲህ አላቸው፣ «እኔ እግዚአብሔርን ስለምፈራ እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አትርፉ።

19- ታማኝ ሰዎች ከሆናችሁ፣ ከመካከላችሁ አንዱ እዚህ እስር ቤት ሲቆይ፣ የቀራችሁት ግን ለተራቡት ቤተሰቦቻችሁ እህል ትወስዱላቸዋላችሁ፤

20- ታናሽ ወንድማችሁን ግን ይዛችሁ መምጣት አለባችሁ፤ በዚህም የተናገራችሁት ቃል እውነተኛነት ይረጋገጣል። እናንተም ከመሞት ትተርፋላችሁ።» እነርሱም ይህንኑ ለመፈጸም ተስማሙ።

- ዮሴፍ ለወንድሞቹ እህል ሰጣቸው ከመካከላቸው አንዱን ብቻ አስቀርቶ ሌሎቹን ወደ ከነዓን ላካቸው።

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ከነዓን ይዘውት የሄዱት እህል አለቀ።

- ስለዚህ የዮሴፍ አባት ልጆቹ ወደ ግብፅ ሄደው ተጨማሪ እህል እንዲገዙ ነገራቸው።

ዘፍጥረት 43፡1-5 እና 11-15

1- ራቡ አሁንም በምድሪቱ ላይ እንደ ጸና ነበር።

2- ከግብፅ ያመጡትንም እህል በልተው ከጨረሱ በኋላ፣ አባታቸው «እስቲ እንደገና ወርዳችሁ፣ ጥቂት እህል ሸምቱልን» አላቸው።

3- ይሁዳ ግን እንዲህ አለው፤ «ያ ሰው <ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም> ብሎ በጥብቅ አስጠንቅቆናል።»

4- ወንድማችን ከእኛ ጋር እንዲወርድ ከፈቀድህ፣ ወደዚያ ሄደን እህል እንሸምትልሃለን፤

5- እርሱን የማትልከው ከሆነ ግን፣ እኛም ወደዚያ አንወርድም፣ ያም ሰው፣ "ወንድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ፣ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም" ብሎናል።»

11- ከዚህ በኋላ አባታቸው እስራኤል እንዲህ አላቸው፤ «ነገሩ እንዲህ ከሆነስ፣ ይህን አድርጉ፡- ምድሪቱ ከምታፈራው ምርጥ ነገሮች ጥቂት በለሳን፣ ጥቂት ማር፣ ሽቱ፣ ከርቤ ተምርና ለውዝ በየስልቻችሁ ይዛችሁ ለዚያ ሰው እጅ መንሻ ውሰዱለት።

12- በየስልቻችሁ አፍ ላይ የተገኘውን ብር መመለስ ስላለባቸው ዕጥፍ ገንዘብ ያዙ፤ ያ በየስልቾቻችሁ ውስጥ የተገኘው ብር ምናልባት በስሕተት የመጣ ሊሆን ይችላል።

13- ወንድማችሁንም ይዛችሁ ወደ ሰውየው በቶሎ ሂዱ።

14- ሌላውን ወንድማችሁንና ብንያምን ይዛችሁ መመለስ እንድትችሉ ሁሉን የሚችል አምላክ በምሕረቱ የዚያን ሰው ልብ ያራራላችሁ። እንግዲህ ልጆቼንም ባጣ ምን አድርጋለሁ፤ ያመጣውን እቀበላለሁ።

15- ሰዎቹም እጅ መንሻውን፥ የብሩን ዕጥፍ እንዲሁም፣ ብንያምን ይዘው ተነሡ፤ ወደ ግብፅም በፍጥነት ወረዱ፤ ዮሴፍም ፊት ቀረቡ።

- የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ተመልሰው ሄዱ።

- ግብፅ እንደ ደረሱ ዮሴፍ ወንድሞቹን በቤቱ ጋበዛቸው።

ዘፍጥረት 42፡16-17

16- ዮሴፍ ብንያምን ከወንድሞቹ ጋር ባየው ጊዜ፣ የቤቱን አዛዥ፣ «እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት ይዘሃቸው ሂድ፤ ዛሬ ቀትር ላይ አብረውኝ ስለሚበሉ ፍሪዳ ተጥሎ ምሳ ይዘጋጅ» አለው።

17- አዛዡም ዮሴፍ የነገረውን አደረገ፤ ሰዎቹንም ወደ ቤት ወሰዳቸው።

- ዮሴፍ ወንድሞቹ አብረው ሳሉ እርሱ ዮሴፍ መሆኑን ገለጠላቸው።

ዘፍጥረት 45፡3-8

3- ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ «እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ ለመሆኑ አባቴ እስካሁን በሕይወት አለ?» ሲል ጠየቃቸው። ወንድሞቹ ግን በፊቱ ተደናግጠው ስለ ነበር፣ መልስ ሊሰጡት አልቻሉም።

4- ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ «እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በሉ» አላቸው። ወደ እርሱም በቀረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ «ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ።

5- አሁንም በመሸጣችሁ አትቆጩ፤ በራሳችሁም አትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል።

6- በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፤ ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ።

7- ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፉ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ።

8- ስለዚህ፣ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር እንጂ እናንተ አይደላችሁም። ፤ እርሱም ለፈርዖን እንደ አባት፣ በቤት ንብረቱ ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ ምድር ላይ ገዥ አደረገኝ።

- ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምን አላቸው?

- ዮሴፍ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ግብፅ እንደ ላከው ነገራቸው።

- ራቡ ገና የሚቀጥል ስለሆነ ወንድሞቹ አባታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ሁሉ ይዘው ከከነዓን ወደ ግብፅ እንዲመጡ ዮሴፍ ነገራቸው።

ዘፍጥረት 45፥9-11

9- «አሁንም በፍጥነት ወደ አባቴ ተመልሳችሁ እንዲህ በሉ፤ ልጅህ ዮሴፍ እንዲህ ይላል፡ «እግዚአብሔር የመላው ግብፅ ጌታ አድርጎኛል፤ ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ ና።

10- ልጆችህን፣ የልጅ ልጆችህን፣ በጎችህን፣ ፍየሎችህን ፣ ከብቶችህንና ያለህን ሁሉ ይዘህ በአቅራቢያዬ በጌሤም ትኖራለህ።

11- ገና ወደፊት የሚመጣ የአምስት ዓመት ራብ ስላለ፣ በዚያ የሚያስፈልጋችሁን እኔ እሰጣችኋለሁ፤ ያለበለዚያ ግን አንተና ቤተሰዎችህ ያንተም የሆነው ሁሉ ችግር ላይ ትወድቃላችሁ።»

- የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ከነዓን ተመለሱ።

- እስቲ ለአባታቸው ለያዕቆብ ምን እንዳሉት አዳምጡ፡-

ዘፍጥረት 45፥25-28

25- እነርሱም ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ምድር ወደሚኖረው ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ መጡ።

26- አባታቸውንም፣ «እነሆ ዮሴፍ በሕይወት አለ! እንዲያውም፣ በግብፅ ምድር ሁሉ ገዥ ሆኖአል» ብለው ነገሩት። ያዕቆብም በድንጋጤ ክው አለ፤ ሊያምናቸው አልቻለም።

27- ነገር ግን ዮሴፍ የነገራቸውን ሁሉ ሲያጫውቱትና እርሱንም ወደ ግብፅ ለማጓጓዝ ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላዎች ሲያይ፣ የአባታቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ።

28- ከዚያም እስራኤል፤ «ልጄ ዮሴፍ በሕይወት አለ፤ ከመሞቴ በፊት ሄጄ ልየው» አለ።

- ስለዚህ የዮሴፍ አባትና ወንድሞቹ ከዮሴፍ ጋር ለመኖር ወደ ግብፅ ሄዱ።

ዘፍጥረት 46፡5

5- ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሣ፤ የእስራኤል ወንዶች ልጆችም አባታቸውን ያዕቆብን ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ፈርዖን ለያዕቆብ ከላካቸው ሠረገላዎች ላይ አወጧቸው።

- ያዕቆብ ቤተ ሰቡን በሙሉ ይዞ ወደ ግብጽ የሄደው ለምንድን ነው?

- የሴፍ ግብጽ ይኖር ስለነበር።

- በግብጽ ብዙ እህል ስለነበር።